የሰበር መ/ቁ. 12025

መጋቢት 18/1999

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አሰግድ ጋሻው

3. መስፍን ዕቁበዮናስ

4. ሂሩት መለሠ

5. ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- አቶ ምናሴ አልማው አልቀረቡም

መልስ ሰጪ፡- ዐቃቤ ሕግ አልቀረበም

ፍ ር ድ

ይህ መዝገብ ለሰበር ችሎት የቀረበው አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሕግ ስህተት መኖሩን በሚያመለክት ሁኔታ የተሰጠ በመሆኑ ውሣኔዎቹ ይሻሩልኝ ሲል በማመልከቱ ነው፡፡

ይህ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ ከስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች እንዲሁም በዚህ ፍርድ ቤት ከተደረገው የጽሑፍ ክርክርና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሕጐች ጋር በማገናዘብ መርምሮአል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች የተከሰሰውና ጥፋተኛ የተባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 656(ሀ) እና (ለ)ን በመተላለፍ ሲሆን ለፍርድ ቤቶቹ ውሣኔ ምክንያት የሆነው አመልካች የጥብቅና ፈቃድ ሣይኖረው የጥብቅና ፈቃድ ያለው በማስመሰል የግል ተበዳዮችን ጉዳይ አስፈጽምላችኋለሁ በማለት ብር 3830 (ሶስት ሺህ ሦስት መቶ ሰላሣ) መወሰዱ በመረጋገጡ ነው፡፡ አመልካች በዚህ ችሎት ማስረጃ አልቀረበብኝም ቢልም የስር ፍርድ ቤቶች በቂ ማስረጃ ቀርቦበት የወሰኑ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይልቁንም አመልካች ቀደም



ሲል ተሰጥቶት የነበረው የጥብቅና ፈቃድ መሠረዙ ከተገለፀለት በኋላ ይህን ድርጊት መፈፀሙ በማስረጃ ተረጋግጦበታል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የመከላከል መብቴ አልተጠበቀልኝም ቢልም ተደጋጋሚ እድል ተሰጥቶት የመከላከያ ማስረጃውን ሊያቀርብ አለመቻሉ ከመዝገቡ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተከሣሹ የመከላከል መብቱ ሕገመንግሥታዊ መብት መሆኑ ባያከራክርም ተከሣሽ በሆነበት ጉዳይ ላይ በተገቢው አጭር ጊዜ ውስጥ የመከላከያ ማስረጃ ካለው እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቶች ተደጋጋሚ ቀጠሮ ቢሰጡም አመልካቹ እድሉን ባለመጠቀሙ ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ሕግ መንግሥታዊ መብት ጣሱ ሊያሰኛቸው አይችልም፡፡ በመሆኑም አመልካች በስር ፍርድ ቤት የቀረበበት ክስ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠበት በመሆኑና የተጣለበት የሁለት ዓመት ቅጣትም ሕጉ በሚያዘው ክልል ውስጥ በመሆኑ ሂደቱም ሆነ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን የሚያሣይ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ው ሣ ኔ

(1) በዚህ ጉዳይ የቀረበው የሰበር ማመልከቻ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

(2) የቤንሻጉል ጉምዝ የከፍተኛና የጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡